## ለ2026 የቻይንኛ-ተናጋሪዎች ዓለም አቀፍ ኮንፍረንስ ቁልፍ መግለጫዎች

የመጽሐፍ ቅዱስ ስድሳ ስድስቱ መጻሕፍት ለአንድ ነገር ብቻ እንደሆነ ኢዮብ ይገልጣል፦
ክርስቶስን እንኖርና ክርስቶስን እንገልጥ ዘንድ ሕይወታችን፣ ባሕርያችን እና ሁሉ ነገራችን ለመሆን
እግዚአብሔር በክርስቶስ እንደ መንፈስ ራሱን ወደ ውስጣችን ለማደሉ፤
ይህ ሕይወታችንን የሚገዛ መርህ መሆን አለበት።

ኖኅ በእግዚአብሔር አመነ፣ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ፣
እግዚአብሔርን ደስ አሰኘ፣ እግዚአብሔር የሆነውንም ሁሉ ተደሰተ።

ብዙዎች የተካተቱበት ክርስቶስ እንደ ድንጋዩና እንደ ተራራው፣
ሙሽራው ከሙሽራይቱ ጋር፣ የእግዚአብሔር እስትንፋስ ያለው ብዙዎች የተካተቱበት የእግዚአብሔር ሰው
በአፉ እስትንፋስ፣ ሰይፍ የክርስቶስን ተቃዋሚና ሠራዊቱን
ያደቃቸዋል፣ ይገድላቸውማል።

በክርስቶስ እግዚአብሔር ወደ ሰው ውስጥ ተቀናብሯል፣
ሰው ወደ እግዚአብሔር ውስጥ ተቀናብሯል፣
እግዚአብሔርና ሰው አንድ አካል ለመሆን ተዋሕደዋል፣
ያም አምላክ-ሰው ይባላል።

*© 2026 Living Stream Ministry*

**ለዓለም አቀፉ የቻይንኛ ተናጋሪዎች ኮንፈረንስ**
**የመልእክቶች አውትላይኖች**
**የካቲት 6-8፣ 2018**

**አጠቃላይ ርዕስ፦**
**ኖኅ፣ ዳንኤል እና ኢዮብ—የእግዚአብሔርን ኢኮኖሚ ለመፈጸም**
**በሕይወት መስመር ላይ የድል ነሺ ሕይወትን የመኖር ምሳሌዎች**

*መልእክት አንድ*

***ዘመኑን ለመቀየር በዘመኑ ራእይ መሠረት መኖር እና መሥራት***

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ ሕዝ. 14፥14፣ 20፤ ዘፍ. 6፥8፤ ማቴ. 24፥37-39፤ ዳን. 2፥34-35፤ ኢዮብ 42፥5-6

**I. ኖኅ፣ ዳንኤል እና ኢዮብ የእግዚአብሔርን ኢኮኖሚ ለመፈጸም በሕይወት መስመር ላይ የድል ነሺ ሕይወትን እንዴት መኖር እንደምንችል የሚገልጡ ምሳሌዎች ናቸው፤ ይህም ዘመኑን ለመቀየር በዘመኑ ራእይ መሠረት መኖር እና መሥራት ነው—ሕዝ. 14፥14፣ 20፤ ዘፍ. 2፥9፤ ራእይ 2፥7፤ 22፥1-2፤ ማቴ. 24፥37-39፣ 45-51፤ ዳን. 2፥34-35፤ ሐዋ. 26፥19፤ 2 ጢሞ. 4፥8።**

**II. የኖኅ፣ የዳንኤል እና የኢዮብ ሕይወቶች ሦስታንዱ አምላክ ዘላለማዊ ኢኮኖሚውን ለመፈጸም ወደ መረጣቸው እና ወደ ዋጃቸው ሕዝቡ ውስጥ ራሱን እንደሚያድል፣ ራሱን እንደሚሠራ ይገልጣሉ፤ መላው መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው ሦስታንዱ አምላክ ለመለኮታዊ ኢኮኖሚው መፈጸም እኛ እርሱን እንድንለማመደው፣ እንድንደሰተው እና እንድንገልጠው ራሱን ወደ እኛ ውስጥ በማደሉ ገዢ መርህ መሠረት ነው— ተዛ. 1 ጢሞ. 1፥3-4፤ ኤፌ. 3፥2፤ 1 ጴጥ. 4፥10፤ መዝ. 36፥8-9፤ 2 ቆሮ. 13፥14፤ ኤፌ. 3፥16-19፦**

ሀ. እግዚአብሔር አብ፣ ክርስቶስ የሆነውን ነገር ሁሉ የሚያሳይ የጥበብ ዓውደ-ርዕይ ያደርጋቸው ዘንድ ሁሉን-ያካተተውን ክርስቶስ ወደ ተመረጡት ሕዝቡ ውስጥ እንደ ጽድቅ፣ ቅድስናና ክብር ለማደል፣ ለግንባታው ያለውን መሻት እና እቅድ እና ቃል ኪዳኑን፣ ቃሉን የሚጠብቅበትን ዘላለማዊ ታማኝነቱን በኖኅ እናየዋለን—ዘፍ. 3፥24፤ 6፥1-14፤ 9፥12-17፤ ሕዝ. 1፥26-28፤ 1 ቆሮ. 1፥9፤ ኤፌ. 2፥10፤ ራእ. 4፥3፤ 21፥19-20።

ለ. በዳንኤል ክርስቶስ ወልድ የእግዚአብሔር እንቅስቃሴ ማዕከል እና አጽናፍ ዓለማዊነት እንደሆነ እና የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ ግብ ይህንን ዘመን ለመዝጋት የእግዚአብሔር ዘመን ቀያሪ መሣሪያ እንዲሆኑና መላ ምድርን የእግዚአብሔር መንግሥት በማድረግ ምድርን ሁሉ ለመሙላት ታላቅ ተራራ እንዲሆኑ ከብዙዎች የሆነውን ክርስቶስ፣ ክርስቶስን ከድል ነሺዎቹ ጋር እንደ የሚፈጨው ድንጋይ ማግኘት እንደሆነ እናያለን—ዳን. 2፥31-45፤ 7፥13-14፤ 10፥4-9፤ ኢዩኤል 3፥11፤ ራእይ 12፥1-2, 5, 11፤ 19፥7-21።

ሐ. በኢዮብ ከብዙዎች ለሆነው የእግዚአብሔር መገለጥ፣ ለእግዚአብሔር ክብር በሕይወት፣ በባሕርይ እና በመልክ ተመላኪነቱን ሳይጨምር እግዚአብሔርን በመሆን በእግዚአብሔር ልብ ውስጥ ያለውን ነገር እንዲያከናውኑ እግዚአብሔር መንፈስ አፍቃሪዎቹ እግዚአብሔርን በማየታቸው እግዚአብሔርን እንዲያገኙ እና በእግዚአብሔር እንዲለወጡ በመንፈስ ቅዱስ ማደስ በመለወጥ ሂደት እነርሱን ማሳለፉን እናያለን—ኢዮብ 10፥13፤ 42፥5-6፤ ኤፌ. 3፥9፤ ማቴ. 5፥8፤ 2ኛ ቆሮ. 3፥16-18፤ ቲቶ 3፥5፤ 1 ቆሮ. 10፥31፤ ኤፌ. 3፥20-21፤ ራእ. 21፥10-11።

**III. "ኖኅ ግን በእግዚአብሔር ፊት [ጸጋን] አገኘ"—ዘፍ. 6፥8፦**

ሀ. የኖኅ ሕይወት እና ሥራ፣ ጸጋ ለወደቀው ሰው ምን ያህል ማድረግ እንደሚችል ይገልጣሉ፤ ጸጋ ለድሰታችን፣ የሸክማችን ተሸካሚ የሆነው በእኛ ምትክ ሁሉን ነገር በእኛ ውስጥ የሚሠራው ድንቁ ክርስቶስ ነው—ቁ. 1-14፤ ማቴ. 24፥37-39፤ 2 ቆሮ. 12፥7-9፦

1. ሥጋ የዲያብሎስ መገኘት ነው፣ ጸጋ የእግዚአብሔር መገኘት ነው፤ የሰይጣንን መገኘት ለመጋፈጥ፣ የእግዚአብሔር መገኘት ያስፈልገናል—ዘፍ. 6፥3፣ 8፤ ሮሜ 7፥17-21፤ ዕብ. 4፥16፤ 1 ቆሮ. 15፥10።
2. የጸጋ ውጤት ጽድቅ ነው፤ በጸጋ ኃይል፣ በጸጋ ብርታት እና በጸጋ ሕይወት ከእግዚአብሔር ጋር፣ እርስ በርሳችን፣ ብሎም ከራሳችን ጋር ትክክል መሆን እንችላለን—ሮሜ 5፥17፣ 21፤ 2 ጴጥ. 2፥5።

ለ. ኖኅ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ፣ ለመለኮታዊው ኢኮኖሚ መከናወንም መርከብን ሠራ—ዘፍ. 6፥8-22፤ ዕብ. 11፥7፤ 1 ጴጥ. 3፥20-21፤ ማቴ. 16፥18፦

1. ክርስቶስ የእግዚአብሔር እና የሰው ግንባታ መሆኑን በማመልከት በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የመጀመሪያው የእግዚአብሔር ግንባታ የኖኅ መርከብ ነው፤ የእግዚአብሔር ግንባታ አምላክ-ሰው ነው—ዮሐ. 1፥14፤ 2፥19፤ 1 ቆሮ. 3፥9፣ 16-17፤ ራእይ 21፥2, 22፤ ኤፌ. 2፥22፤ መዝ. 27፥4።
2. የመርከቡ መገንባት እንደ የግንባታ ዕቃ በክርስቶስ ብልጥግናዎች ንጥረ-ነገር የሚገነባውን ከብዙዎች የሆነውን ክርስቶስን፣ የክርስቶስ አካል የሆነችውን ቤተ ክርስቲያንን በምሳሌ ያሳያል—ማቴ. 16፥18፤ 1 ቆሮ. 3፥9-12፤ ኤፌ. 3፥8-10፤ 4፥12።

3. የመርከቡ ሦስት ፎቆች በእርሱ ልምምዳችን መሠረት ሦስታንዱን አምላክ ያመለክታሉ፤ በታችኛው ፎቅ የተመለከተው መንፈስ ወደ ወልድ ያመጣናል (1 ጴጥ. 1፥2፤ ዮሐ. 16፥8፣ 13-15)፣ ወልድ ደግሞ በልምምዳችን ከፍ ወዳለ ደረጃ ወደ አብ ያመጣናል (14፥6፤ ኤፌ. 2፥18፤ 1 ዮሐ. 1፥5፤ 4፥8)።
4. በመርከቡ ሦስተኛ ፎቅ ላይ ወደ ሰማይ አቅጣጫ የሆነ አንድ መስኮት ብቻ ነበር፤ ይህም በቤተ ክርስቲያን፣ በእግዚአብሔር ግንባታ ውስጥ በአንዱ የአዲስ ኪዳን አገልግሎት በኩል አንድ መገለጥ እና አንድ ራእይ ብቻ እንዳለ ያመለክታል—ዘፍ. 6፥16፤ ሐዋ. 26፥19፤ ምሳ. 29፥18፤ 1 ጢሞ. 1፥3-4፤ 2 ቆሮ. 3፥6-9፤ 4፥1።

## IV. እንደ የግል ሀብቱ የውድነት ሰዎች ብሎም ውድነት ራሱን እንሆን ዘንድ ክርስቶስን እንደ የእግዚአብሔር የላቀው ውድነት ለመደሰት ጊዜውን መዋጀት እንዳለብን ዳንኤል ያሳየናል—ዳን. 9፥23፤ 10፥11፣ 19፤ 1 ጴጥ. 2፥7፤ ዘጸ. 19፥4-6፦

ሀ. የላቀው ክርስቶስ ለዳንኤል አድናቆት፣ መጽናናት፣ መበረታታት፣ መጠባበቅ እና መጽናት በላቀው ውድነቱ እንደ ሰው ተገለጠለት—ዳን. 10፥4-9፦
1. ክርስቶስ በምርኮ የነበሩትን የተመረጡ ሕዝቡን ለመንከባከብ በበፍታ በተመሰለው በስብዕናው እንደ ካህን ተገለጠ—ቁ. 5፤ ዘጸ. 28፥31-35።
2. ክርስቶስ በሰዎች ሁሉ ላይ ለመግዛት በወርቅ መታጠቂያ በተመሰለው በመለኮትነቱ በንግሥናው ተገለጠ—ዳን. 10፥5።
3. አካሉ ቢረሌ በመምሰሉ እንደተመለከተው ለሕዝቡ መደነቅ ክርስቶስ በውድነቱ እና የተከበረ በመሆኑ ተገለጠ፤ ቢረሌ የሚለው የዕብራይስጥ ቃል ሰማያዊ-አረንጓዴ ወይም ቢጫ የከበረ ድንጋይን ሊያመለክት ይችላል፤ ይህም ክርስቶስ አካል በመልበሱ መለኮታዊ (ቢጫ)፣ ሕይወት የተሞላ (አረንጓዴ) እና ሰማያዊ (ሰማያዊ) መሆኑን ያመለክታል—ቁ. 6።
4. በተጨማሪም ክርስቶስ ፊቱ እንደ መብረቅ ምስያ በመሆኑ እንደተመለከተው (ቁ. 6) በሕዝቡ ላይ ለማብራት በብሩህነቱ እና ዓይኖቹ እንደ ሚንበለበል ፋና በመሆናቸው እንደተመለከተው ለመመርመር እና ለመፍረድ አብርሆት በሚሰጥ እይታው ተገለጠ።
5. ክርስቶስ፣ እንደሚያብረቀርቅ የጋለ ናስ በሆኑት ክንዶቹና እግሮቹ እንደተመለከተው በሥራው እና በእንቅስቃሴው ማብረቅረቅ ተገለጠ—ቁ. 6።
6. ክርስቶስ፣ የቃሉ ድምፅ እንደ ብዙ ሕዝብ ድምፅ በመሆኑ እንደተመለከተው፣ በሰዎች ላይ ለመፍረድ በጠንካራ ንግግሩ ተገለጠ—ቁ. 6።

ለ. በነገር ሁሉ ለክርስቶስ ቀዳሚውን ስፍራ፣ የመጀመሪያውን ስፍራ ለመስጠት፣ መላው የዓለም ሁኔታ በሰማያት አምላክ ሰማያዊ አገዛዝ ሥር የመሆኑን መገለጥ ዳንኤል ተቀበለ—2፥34-35, 44-45፤ 7፥9-10፤ 4፥34-35፤ ቆላ. 1፥15, 17-18፤ ራእይ 2፥4-5።

## V. "እግዚአብሔርም...ለኢዮብ መለሰ" (ኢዮብ 38፥1)፤ "ኢዮብም መለሰ እግዚአብሔርንም እንዲህ አለው" (ኢዮብ 42፥1)፤ "እግዚአብሔርም ምርኮውን መለሰለት" (ቁ. 10)፦

ሀ. የኢዮብ መከራዎች የእግዚአብሔር ፍርድ ጉዳይ እንደነበሩ በማሰባቸው የኢዮብ ጓደኞች አመክንዮ በመልካምና ክፉ እውቀት ዛፍ መስመር መሠረት ነበር፤ ሆኖም፣ የኢዮብ መከራዎች ኢዮብ እግዚአብሔርን ይበልጥ ያገኝ ዘንድ እግዚአብሔር እርሱን ለማግኘት የእግዚአብሔር መጨረስ ነበሩ—9፥15፤ 11፥12፤ 13፥4፤ ፊልጵ. 3፥8፤ 12-13።
1. እግዚአብሔር በኢዮብ ላይ የነበረው ውጥን በእግዚአብሔር ባሕርይ የታደሰ ኢዮብን ይገነባ ዘንድ የተፈጥሯዊውን ኢዮብ የራስ ፍጹምነትና ቅንነት ማፈራረስ ነበር—ኢዮብ 1፥1፤ ቲቶ 3፥5።
2. የእግዚአብሔር ውጥን ኢዮብ በስብዕና ሕይወቱ የጎደለው ነገር እግዚአብሔር ራሱ መሆኑን እንዲገነዘብ እና እግዚአብሔርን እንዲከታተል፣ እንዲያገኝ እና እንዲገልጥ ኢዮብን ጥልቅ ወደ ሆነ እግዚአብሔርን መፈለግ ማስገባት ነበር—ቆላ. 2፥19።
3. የእግዚአብሔር ውጥን በሕይወት ዛፍ መስመር ላይ ያለ ኢዮብን ማግኘት እና ኢዮብን የእግዚአብሔር ሰው ማድረግ ነበር—ዘፍ. 2፥9፤ 1 ጢሞ. 6፥11፤ 2 ጢሞ. 3፥17፤ ኤፌ. 3፥14-21።

ለ. ኢዮብ ስልሳ ስድስት መጻሕፍት ያሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ለአንድ ነገር ብቻ እንደሆነ ይገልጣል፦ ክርስቶስን እንድንኖር እና ክርስቶስን እንድንገልጥ ሕይወታችን፣ ባሕርያችን እና ሁሉ ነገራችን ለመሆን እግዚአብሔር በክርስቶስ በመንፈስ በኩል ራሱን ወደ እኛ ውስጥ ማደሉ ነው፤ ይህ ሕይወታችንን የሚገዛ መርህ ሊሆን ይገባል—ኢዮብ 10፥13፤ ኤፌ. 3፥9፤ ፊልጵ. 3፥8-9፤ ኤፌ. 1፥22-23፤ 2፥15፤ ራእ. 21፥2።

ሐ. በዚህ መርህ ለመኖር እና ለመሥራት መንገዱ መንፈሳችንን በማንቀሳቀስ በመንፈስ፣ ከመንፈስ ጋር፣ በመንፈስ ውስጥ እና በመንፈስ በኩል መሆን እና ሁሉንም ነገር ማድረግ ነው—ገላ. 5፥25፤ ሮሜ 8፥4፤ ፊልጵ. 3፥3፤ ራእ 2፥7፤ 22፥17።

© 2026 Living Stream Ministry

መልእክት ሁለት

**የሕይወት መስመር በኖኅ ዘንድ—**
**ዘመኑን የሚቀይር ኑሮና ሥራ**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ ዘፍ. 6፥5-14፤ ዕብ. 11፥7

**I. ኖኅ በእግዚአብሔር አመነ፣ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ፣ እግዚአብሔርን ደስ አሰኘ፣ እግዚአብሔር የሆነውንም ሁሉ ተደሰተ፦**

ሀ. ሰይጣን ሰውን ፍጽሞ አበላሽቶ ነበር፤ እግዚአብሔርም ለዓላማው የፈጠረውን ሰው ለማጥፋት ቆርጦ ነበር።

ለ. ከዚህም የተነሣ፣ እግዚአብሔር የተሸነፈ ይመስል ነበር፤ *ኖኅ ግን* የሚለው እግዚአብሔር ከሰው ጋር የነበረውን የመጀመሪያውን ዓላማ ማከናወኑን ይቀጥል ዘንድ ለእግዚአብሔር መንገድ የሰጠውን ሉዓላዊ መንስኤ ይጠቁማል።

ሐ. በኖኅ ሕይወትና ሥራ በኩል፣ እግዚአብሔር በጠላቱ ላይ ድልን ተቀዳጀ፤ ዘመኑንም ቀየረ።

**II. የኖኅ ኑሮ ዘመኑን የቀየረ ኑሮ ነበር—ተዛ. ፊልጵ. 1፥19-21፦**

ሀ. ዘመኑን የሚቀይር ኑሮ የቀደሙ አባቶችን እግዚአብሔርን የመምሰል መንገዶች የሚወርስ ኑሮ ነው፦

1. ኖኅ ክርስቶስ የሴቲቱ ዘር የመሆኑን የተስፋ ቃል እና እግዚአብሔርን እንደሚያረካው ጽድቅ የክርስቶስን መሸፈን በመቀበል የአዳምን የመዳን መንገድ ወርሷል—ዘፍ. 3፥15፤ 20-21፤ ተዛ. ኢሳ. 12፥2።
2. ኖኅ ክርስቶስን ለኃጢአቶቻችን እንደሆነ መሥዋዕት ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርን ለማስደሰት እንደሆነ ስጦታ ለእግዚአብሔር የማቅረብን የአቤልን የመሠዋት መንገድ ወርሷል—ዘፍ. 4፥4።
3. ኖኅ [ያሕዌ] የሆነውን ሁሉ ለመደሰት የያሕዌን ስም የመጥራትን የሄኖስን መንገድ ወርሷል—ቁ. 26፤ ኤር. 33፥3፤ ሮሜ 10፥12፤ 2 ጢሞ. 2፥22።
4. ኖኅ እግዚአብሔርን እንደ ማዕከላችን እና እንደ ሁሉ ነገራችን መውሰድን፣ በእግዚአብሔር መሠረትና ከእግዚአብሔር ጋር መኖርና ሁሉንም ነገሮች ማድረግ የሆነውን አካሄድን ከእግዚአብሔር ጋር የማድረግን የሄኖክን አካሄድ ወርሷል—ዘፍ. 5፥22-24፤ ዕብ. 11፥5-6፤ 2 ቆሮ. 5፥4፣ 9፣ 14-16፤ 6፥1።

ለ. ኖኅ እየኖረበት የነበረውን የተበላሸ ዘመን እውነተኛ ሁኔታ እግዚአብሔር አሳየው —ዘፍ. 6፥3፣ 5፣ 11፣ 13፤ ማቴ. 24፥37-39፤ 2 ጢሞ. 3፥1-5።

ሐ. "ኖኅ *ግን* በእግዚአብሔር ፊት ሞገስን [ጸጋን] አገኘ"—ዘፍ. 6፥8፦

1. ሰይጣን ሁኔታውን ለማበላሸት የተቻለውን ሁሉ ባደረገበት ጊዜ፣ ሁልጊዜም ዘመኑን የቀየሩ በእግዚአብሔር ፊት ጸጋን ያገኙ ሰዎች ነበሩ—ተዛ. ዳን. 1፥8፤ 9፥23፤ 10፥11፣ 19።
2. የዘፍጥረት ዘገባ ዋና ዓላማ ውድቀትን ለማሳየት ሳይሆን የእግዚአብሔር ጸጋ ለወደቁ ሰዎች ምን ያህል ማድረግ እንደሚችል ለማሳየት ነው፦
   ሀ. ጸጋ ሁሉን ነገር ይሆንልን ዘንድ እና ሁሉን ነገር በእኛ ውስጥ፣ በእኛ በኩልና ለእኛ ያደርግ ዘንድ የተደሰትነው የእግዚአብሔር መገኘት ፣ እግዚአብሔር ራሱ ነው—ዮሐ. 1፥14፤ 16-17፤ ራእ. 22፥21።
   ለ. ጌታን እንደ ጸጋ መደሰት ያለው እርሱን ከሚወዱት ጋር ነው—ኤፌ. 6፥24፤ ዮሐ. 21፥15-17።
   ሐ. የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ጸጋ እንደ የሦስታንዱ አምላክ የተትረፈረፈ አቅርቦት የምንደሰተው የስብዕና መንፈሳችንን በማንቀሳቀስ ነው—ዕብ. 10፥29፤ ገላ. 6፥18፤ ፊልጵ. 4፥23፤ ፊልሞ. 25፤ 2 ጢሞ. 4፥22።
   መ. የእግዚአብሔር ቃል የጸጋ ቃል ነው—ሐዋ. 20፥32፤ ቆላ. 3፥16፤ ተዛ. ኤር. 15፥16።
   ሠ. በሂደት ያለፈውን ሦስታንዱን አምላክ እንደ የሕይወት ጸጋ የምንለማመደው በአንድነት መቆሚያ ስፍራ ላይ ከቅዱሳን ጋር በመሰብሰብ ነው—መዝ. 133፥3፤ 1 ጴጥ. 3፥7፤ ሐዋ. 4፥33፤ 11፥23።
   ረ. ጌታን እንደሚጨምር እና ለሁሉ እንደሚበቃ ጸጋችን በመከራዎችና በፈተናዎች ውስጥ መለማመድ እንችላለን—2 ቆሮ. 12፥9።
   ሰ. በጸጋው ኃይል ለጌታ መድከም ያስፈልገናል—1 ቆሮ. 15፥10፣ 58፤ 3፥12።
   ሸ. የእግዚአብሔር ልዩ ልዩ ጸጋ ደጋግ መጋቢዎች መሆን ያስፈልገናል—1 ጴጥ. 4፥10፤ ኤፌ. 3፥2፤ 2 ቆሮ. 1፥15፤ ኤፌ. 4፥29።
   ቀ. በጸጋ ኃይል፣ በጸጋ ብርታት እና በጸጋ ሕይወት፣ ከእግዚአብሔር ጋርና አንዳችን ከሌላችን ጋር ትክክል መሆን እንችላለን፤ ጸጋ ጽድቅን ያፈራል—ዕብ. 11፥7፤ ሮሜ 5፥17፣ 21።

**III. የኖኅ ሥራ ዘመኑን የቀየረ ሥራ ነበር—1 ቆሮ. 3፥9፤ 2 ቆሮ. 6፥1፤ ማቴ. 16፥18፤ 1 ቆሮ. 3፥12፦**

ሀ. እግዚአብሔር ለኖኅ ሁሉን ያካተተ መገለጥ፣ ተጨማሪ መገለጥ፣ እግዚአብሔር የተበላሸውን ትውልድ የሚያስወግድበትን እና አዲስን ዘመን የሚያመጣበት መንገድ የነበረውን መርከቡን የመገንባት መገለጥ ሰጠው፦

1. መርከቡ የክርስቶስ ምሳሌ ነው (1 ጴጥ. 3፥20-21)—የክርስቶስ ብቻ ሳይሆን በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም የሚጠናቀቀው የክርስቶስ አካል እና አዲሱ ሰው የሆነው ከብዙዎች የሆነው ክርስቶስ፣ የቤተ ክርስቲያንም [ምሳሌ] ነው (ማቴ. 16፥18፤ 1 ቆሮ. 12፥12፤ ኤፌ. 2፥15-16፤ ቆላ. 3፥10-11፤ ራእ. 21፥2)።
2. የመርከቡ መገንባት፣ እንደ ግንባታ ዕቃ በክርስቶስ ብልጥግናዎች ንጥረ-ነገር ከእግዚአብሔር ጋር አብሮ በሚሠሩት የሚገነባውን ከብዙዎች የሆነውን ክርስቶስ በምሳሌ ያሳያል—1 ቆሮ. 3፥9-12፤ ኤፌ. 4፥12፤ 2፥22።
3. ይህ ግንባታ የእግዚአብሔር በሥጋ መገለጥ ይሆኑ ዘንድ ሰዎችን በክርስቶስ አንድ ላይ ለመገንባት ክርስቶስ ወደ እነርሱ ውስጥ መሠራቱ ነው—1 ጢሞ. 3፥15-16፦
   - ሀ. በሥራችን ውስጥ ወሳኙ ጉዳይ ሦስታንዱ አምላክ ራሱን ወደ ማንነታቸው ውስጥ ይገነባ ዘንድ የሚገነባውንና የተገነባውን አምላክ ወደ ሌሎች ውስጥ ማገልገል ነው—ማቴ. 16፥18፤ ኤፌ. 2፥21-22፤ 3፥17፤ 1 ቆሮ. 14፥4።
   - ለ. አንድን ነገር በተግባር መለማመድ ያስፈልገናል—ራሱን ወደ ውስጡ ሰዋቸው ውስጥ ይገነባ ዘንድ በሂደት ያለፈውንና የተጠናቀቀውን ሦስታንዱን አምላክ ወደ ሌሎች ውስጥ ማገልገል፤ ጌታ በዚህ መንገድ እንሠራ ዘንድ እንዲያስተምረን መጸለይ ያስፈልገናል—2 ቆሮ. 13፥14፤ 1 ቆሮ. 3፥9፣ 10፣ 12፤ ሮሜ 11፥36።

ለ. ቤተ ክርስቲያንን በመገንባትና ወደ ቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ በመግባት፣ በታላቁ መከራ በዛሬው ክፉ ትውልድ ላይ ከሚሆነው ከእግዚአብሔር ፍርድ እንድናለን፣ ወደ አዲስ ዘመን፣ ወደ ሺው ዓመት ዘመን ለመግባትም ከዚያ ትውልድ እንለያለን—ዕብ. 11፥7፤ ማቴ. 24፥37-39፤ ሉቃ. 17፥26-27።

© 2026 Living Stream Ministry

መልእክት ሦስት

## በዳንኤልና በባልንጀሮቹ የታየው የድል ነሺዎቹ ድል

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ ዳን. 1—6

I. **የጌታ ምለሳ መርህ እንደ ድል ነሺዎች በሰይጣን መሳሪያዎች ላይ በተቀዳጁት ድል ከእግዚአብሔር ጋር ፈጽመው አንድ በነበሩት "በዳንኤልና ባልንጀሮቹ" (አናንያ፣ ሚሳኤልና አዛርያ) ታይቷል—ዳን. 2፥13፣ 17፤ ተዛ. ራእ. 17፥14፤ ማቴ. 22፥14፦**

ሀ. ዳንኤልንና ባልንጀሮቹን [በፈተናቸው] ዲያብሎሳዊ ፈተናው ናቡከደነፆር የእግዚአብሔር መሆናቸውን የሚያመለክቱትን ስሞቻቸውን ከጣዖታት ጋር አንድ ወዳደረጓቸው ስሞች ቀየራቸው—ዳን. 1፥6-7።

ለ. ትርጉሙ "እግዚአብሔር ፈራጄ ነው" የሆነው ዳንኤል የሚለው ስም "የቤል ልዑል" ወይም "በቤል የተወደደ" የሚል ትርጉም ወዳለው ብልጣሶር ተቀየረ—ኢሳ. 46፥1።

ሐ. ትርጉሙ "እግዚአብሔር በጸጋው ሰጠ" ወይም "በእግዚአብሔር የተወደደ" የሆነው አናንያ የሚለው ስም "በፀሐይ አምላክ አብርሆት ያገኘ" የሚል ትርጉም ወዳለው ሲድራቅ ተቀየረ።

መ. ትርጉሙ "እግዚአብሔር የሆነውን የሆነ ማነው?" የሆነው ሚሳኤል የሚለው ስም "ሻክ እንደምትባለው ጣዖት ማን ሊሆን ይችላል?" የሚል ትርጉም ወዳለው ሚሳቅ ተቀየረ።

ሠ. ትርጉሙ "እግዚአብሔር ረድቷል" የሆነው አዛርያ የሚለው ስም "የእሳት አምላክ ኔጎ ታማኝ አገልጋይ" የሚል ትርጉም ወዳለው አብድናጎ ተቀየረ።

II. **ዳንኤልና ባልንጀሮቹ በአጋንንታዊው መብል ላይ አሸናፊዎች ነበሩ—ዳን. 1፦**

ሀ. የናቡከደነፆር ዲያቢሎሳዊ ፈተና በመጀመሪያ ከእግዚአብሔር የተሸነፉ ምርጦች መካከል አራቱን ብሩህ ወጣት ልጆች፣ ዳንኤልንና ባልንጀሮቹን፣ የእርሱን ርኩስ ምግብ፣ ለጣዖታት የተሠዋን ምግብ በመብላት እንዲረክሱ ማባበል ነበር።

ለ. ለዳንኤልና ለባልንጀሮቹ ያንን ምግብ መብላት ማለት ርኩሰቱን፣ ጣዖታቶቹን ወደ ውስጣቸው መውሰድ ከዚህም የተነሣ ከሰይጣን ጋር አንድ መሆን ነበር—ተዛ. 1 ቆሮ. 10፥19-21።

ሐ. ዳንኤልና ባልንጀሮቹ የናቡከደነፆርን ርኩስ ምግብ መብላት እምቢ ብለው በምትኩ አትክልቶችን መብላት በመረጡ ጊዜ (ዳን. 1፥8-16)፣ በመርህ ደረጃ የመልካምና የክፉ እውቀት ዛፍን ትተው (ተዛ. ዘፍ. 3፥1-6) ከእግዚአብሔር ጋር አንድ እንዲሆኑ ያደረጋቸውን የሕይወትን ዛፍ ወሰዱ (ተዛ. 2፥9፣ 16-17)።

መ. የጌታ ምለሳ ለቤተ ክርስቲያን መገንባት ኢየሱስን የመብላት ምለሳ ነው—ቁ. 9፣ 16-17፤ ራእ. 2፥7፣ 17፤ 3፥20።

ሠ. ቃሎቹን በመብላትና በንጹሕ ልብ እርሱን ከሚጠሩት ጋር ለመገናኘትና አብሮ ለመሆን በመጠንቀቅ ኢየሱስን መብላት እንችላለን—ኤር. 15፥16፤ 2 ጢሞ. 2፥22፤ 1 ቆሮ. 15፥33፤ ምሳ. 13፥20።

III. **ዳንኤልና ባልንጀሮቹ በስብእና ታሪክ ውስጥ እንዳለ መለኮታዊ ታሪክ ታላቁን የሰው ምስልና የሚፈጨውን ድንጋይ ከማየት ሰዎችን በሚከለክለው ዲያብሎሳዊ ማሳወር ላይ አሸናፊዎች ነበሩ—ዳን. 2፦**

ሀ. ከብዙዎች የሆነው ክርስቶስ እንደ ድንጋዩና እንደ ተራራው፣ ሙሽራው ከሙሽራይቱ ጋር፣ የእግዚአብሔር እስትንፋስ ያለው ከብዙዎች የሆነው የእግዚአብሔር ሰው፣ በአፉ እስትንፋስ፣ ሰይፍ የክርስቶስ ተቃዋሚውንና ሠራዊቱን ይፈጫል፣ ያርድማል—ቁ. 34-35፣ 44-45፤ 2 ተሰ. 2፥8፤ ራእ. 19፥11-21፤ ዘፍ. 11፥4-9፤ ተዛ. ኢሳ. 33፥22።

ለ. ለግንባታው ወደ ሕያውና ከቡር ድንጋይነት ይለውጠን ዘንድ ክርስቶስ እንደ ሕያውና ከቡር ድንጋይ፣ እንደ የእግዚአብሔር ሕንጻ የመሠረት ድንጋይ፣ የማዕዘን ድንጋይና የመደምደሚያ ድንጋይ፣ በራሱ እንደ ውድነት ይሰርጸናል—1 ጴጥ. 2፥4-8፤ ኢሳ. 28፥16፤ ዘካ. 3፥9፥ 4፥7፣ 9-10።

IV. **ዳንኤልና ባልንጀሮቹ በጣዖት አምልኮ ማባበል ላይ አሸናፊዎች ነበሩ—ዳን. 3፤ ተዛ. ማቴ. 4፥9-10፦**

ሀ. ዳግም የተወለደው መንፈሳችን ውስጥ ያለው እውነተኛው አምላክ ያልሆነው ነገር ሁሉ እግዚአብሔርን የሚተካ ጣዖት ነው፤ በመንፈስ ውስጥ ያልሆነና ከመንፈስ ያልሆነ ነገር ሁሉ ጣዖት ነው—1 ዮሐ. 5፥21።

ለ. የአካሉ ጠላት በራስ ፍላጎቱ፣ ራስን ከፍ በማድረጉ፣ ራስን በማክበሩ፣ ራስን በማስዋቡና በራስ ጥንካሬው እግዚአብሔርን የሚተካው እኔነት ነው፤ በአካሉ ውስጥና ለአካሉ እኔነትን እንክዳለን፣ ራሳችንን ሳይሆን ክርስቶስ ኢየሱስ ጌታ እንደሆነም እንሰብካለን—ማቴ. 16፥24፤ 2 ቆሮ. 4፥5።

ሐ. የዳንኤል ባልንጀሮች እውነተኛ የሰማዕትነት መንፈስ ነበራቸው፤ በናቡከደነፆር ትእዛዝ በሚነድድ እቶን እሳት ውስጥ ቢጣሉም በሕይወታቸው በመወራረድ ልዩና ብቸኛው አምላክ ለሆነው ለጌታ እና ከጣዖት አምልኮ በተጻራሪ ቆሙ—ዳን. 3፥19-23።

መ. ናቡከደነፆር ወደ እቶኑ እሳት ሲመለከት፣ በእሳቱ መካከል የሚመላለሱ አራት ሰዎች ተመለከተ (ቁ. 24-25)፤ አራተኛው መከራ እየተቀበሉ ካሉትና ስደት ከደረሰባቸው ሦስቱ ድል ነሺዎቹ ጋር ለመሆንና እሳቱን ለመንቀሳቀስ ደስ የሚያሰኝ ስፍራ ለማድረግ የመጣው የላቀው ክርስቶስ እንደ የሰው ልጅ ነበር።

ሠ. ሦስቱ ድል ነሺዎች ከእቶኑ እሳት እንዲያድናቸው እግዚአብሔርን መጠየቅ አላስፈለጋቸውም (ተዛ. ቁ. 17)፤ ክርስቶስ እንደ የሰው ልጅ—በነገር ሁሉ ለእግዚአብሔር ሕዝብ ለማዘን ብቁ እንደሆነውና እንደተካነው ማንነት (ዕብ. 4፥15-16)— ባልንጀራቸው ሊሆንና በመገኘቱ የመከራ ስፍራቸውን ደስ የሚያሰኝ ሁኔታ ሊያደርግላቸው በመከራቸው ሊንከባከባቸው መጣ።

## V. ዳንኤልና ባልንጀሮቹ ሰዎች በሰማያት አምላክ የሰማያትን መግዛት እንዳያዩ በሚከለክለው መሸፈኛ ላይ አሸናፊዎች ነበሩ—ዳን. 4፡-

ሀ. ክርስቶስ ቀዳሚ ይሆን ዘንድ ለእርሱ ሕዝብ ለመሆን በእግዚአብሔር እንደተመረጡ ሰዎች፣ ክርስቶስን ቀዳሚ ለማድረግ ዓላማ በእግዚአብሔር ሰማያዊ አገዛዝ ሥር ነን—ቁ. 18፣ 23-26፣ 30-32፤ ሮሜ 8፥28-29፤ ቆላ. 1፥18፤ 2 ቆሮ. 10፥13፣ 18፤ ኤር. 9፥23-24።

ለ. “በትዕቢትም የሚሄዱትን ያዋርድ ዘንድ ይችላልና”—ዳን. 4፥37።

## VI. ዳንኤልና ባልንጀሮቹ በእግዚአብሔር ፊት መጠጥ ከማብዛት እና ቅድስናው ከመሰደቡ የተነሳ በነበረው ቸልተኝነት ላይ አሸናፊዎች ነበሩ—ምዕ. 5፡-

ሀ. በኢየሩሳሌም ባለው በቅዱስ መቅደሱ ለእግዚአብሔር አምልኮ የነበሩትን ዕቃዎች ብልጣሶር ወስዶ ጣዖታትን ለማምለክ መጠቀሙ ለእግዚአብሔር ቅድስና ስድብ ነበር (ቁ 4)፤ ከናቡከደነፆር ልምምድ ትምህርት መማር ነበረበት (4፥18-37)፤ ሆኖም፣ ትምህርቱን አልተማረም፣ በዚህም ምክንያት መከራ ተቀበለ (5፥18፣ 20፣ 24-31)።

ለ. “መልካም መንፈስ፣ እውቀትም፣ ማስተዋልም፣ ሕልምን መተርጎም፣ እንቆቅልሽንም መግለጥ፣ የተቋጠረንም (ቃል በቃል ሲተረጎም፣ ቋጠሮ) መፍታት...በዳንኤል ዘንድ ተገኝቶአልና”—ቁ. 12።

ሐ. “ብልጣሶር ሆይ...ይህን ሁሉ እያወቅህ በሰማይ ጌታ ላይ ኮራህ እንጂ ልብህን አላዋረድህም። የመቅደሱንም ዕቃዎች በፊትህ አመጡ፣ አንተም መኳንንትህም ሚስቶችህም ቁባቶችህም የወይን ጠጅ ጠጣችሁባቸው ከብርና ከወርቅም ከናስና ከብረትም ከእንጨትና ከድንጋይም የተሠሩትን የማያዩትም የማይሰሙትንም የማያውቁትንም አማልክት አመሰገንህ፤ ትንፋሽህንና መንገድህን ሁሉ በእጁ የያዘውን አምላክ አላከበርኸውም”—ቁ. 22-23፤ ተዛ. ቁ. 20።

## VII. ዳንኤልና ባልንጀሮቹ ድል ነሺዎች በእግዚአብሔር አምልኮ ውስጥ ያላቸውን ታማኝነት በከለከለው ስውር ተንኮል ላይ አሸናፊዎች ነበሩ—ምዕ. 6፡-

ሀ. የዳንኤል 6 ማዕከል ለእግዚአብሔር ኢኮኖሚ መከናወን የሰው ጸሎት ነው፤ ሰው ሊያደርገው የማይችለውን ለማድረግና ሰው ሊረዳው የማይችለውን ለመረዳት ዳንኤል በጸሎት ላይ ተደገፈ፤ ከጸሎት ውጭ የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ወደ ሙላትና ወደ ፍጻሜ የሚመጣበት ሌላ መንገድ የለም፤ የዚህ ምዕራፍ ውስጣዊ ምስጢር ይህ ነው።

ለ. ዳንኤል መስኮቶቹ ወደ ኢየሩሳሌም ተከፍተው በየቀኑ ለሦስት ጊዜ ጸለየ፤ በእርሱ የርኅራኄ ጸሎት በኩል እግዚአብሔር እስራኤልን ወደ አባቶቻቸው ምድር መለሳቸው (ቁ. 10፤ ተዛ. 1 ነገ 19፥12፣ 18)፤ ጸሎታችን የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ ግብ ወደ ሆነው ወደ ክርስቶስ (በቅድስቲቱ ምድር እንደተመሰለው)፣ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት (በቅድስቲቱ ከተማ እንደተመሰለው) እና ወደ እግዚአብሔር ቤት (በቅዱሱ መቅደስ እንደተመሰለው) ሲሆን እግዚአብሔር ጸሎታችንን ይሰማል—8፥48-49።

© 2026 Living Stream Ministry

መልእክት አራት

## ኢዮብ እና ሁለቱ ዛፎች

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ ዘፍ. 2፥9፣ 17፤ ራእ. 22፥1-2፣ 14፤ ኢዮ. 1፥1፤ 2፥3፤ 42፥1-6

### I. በመለኮታዊው መገለጥ ውስጥ ሁለት ዛፎች፣ ሁለት ምንጮች፣ ሁለት መንገዶች፣ ሁለት መርሆች እና ሁለት መጠናቀቆች አሉ፦

ሀ. ሁለት ዛፎች፦

1. የሕይወት ዛፍ ሰው ከሦስታንዱ አምላክ ጋር ባለው ግንኙነት ሦስታንዱ አምላክ ለሰው ሕይወት መሆኑን ያመለክታል—ዘፍ. 2፥9፤ መዝ. 36፥9።
2. የመልካም እና የክፉ እውቀት ዛፍ ሰው በእግዚአብሔር ፊት በመውደቁ ሰይጣን፣ ዲያብሎስ፣ ክፉው ለሰው ሞት መሆኑን ያመለክታል—ዘፍ. 2፥17።

ለ. ሁለት ምንጮች፦

1. የሕይወት ዛፍ ለአቅርቦታቸው እና ለድሰታቸው እግዚአብሔርን እንደ ሕይወት ለሚሹ ሰዎች ምንጭ ነው—ዮሐ 1፥4፤ 15፥1።
2. የመልካም እና የክፉ እውቀት ዛፍ  ወደ ሞትና የዘላለም ጥፋት ሰይጣንን እንደ መርዛቸው የሚከተሉ ሰዎች ምንጭ ነው—8፥44።
3. የእነዚህ ሁለት ምንጮች ውጤት ሁለት መንግሥታት ናቸው—የእግዚአብሔር መንግሥት እና የሰይጣን መንግሥት— ማቴ. 21፥43፤ 12፥26፤ ቆላ. 1፥13።

ሐ. ሁለት መንገዶች፦

1. የመጀመሪያው መንገድ፣ እንደ አቅርቦት በዘላለማዊ ሕይወቱ ሰዎች እግዚአብሔርን እንዲፈልጉ፣ እግዚአብሔርን እንዲያገኙና እግዚአብሔርን እንዲደሰቱ ቀጭኑ መንገድ፣ የሕይወት መንገድ ነው—ማቴ. 7፥14፤ ሐዋ. 9፥2፤ 16፥17፤ 18፥25-26፤ 2 ጴጥ. 2፥15፣ 21።
2. ሁለተኛው መንገድ የሰይጣን ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሰዎች ሰይጣንን እንዲከተሉ ሰፊው መንገድ፣ የሞት እና የመልካምና ክፉ መንገድ ነው—ማቴ. 7፥13፤ 1 ዮሐ. 3፥10።

መ. ሁለት መርሆች፥-

1. የመጀመሪያው መርህ የሕይወት መርህ—በእግዚአብሔር ላይ ጥገኛ የመሆን መርህ ነው—ዮሐ. 15፥5፤ ዘፍ. 4፥4።
2. ሁለተኛው መርህ የሞት እና የመልካምና ክፉ መርህ—ከእግዚአብሔር ኢ-ጥገኛ የመሆን መርህ ነው—ኤር. 17፥5-6፤ ዘፍ. 4፥3።

ሠ. ሁለቱ መጠናቀቆች ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው ግንኙነት የሚወስዷቸው የሁለቱ መንገዶች የመጨረሻ ውጤት ናቸው፦

1. የእግዚአብሔር የሕይወት መንገድ መጠናቀቅ የሕይወት ውኃ ከተማ፣ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ናት—ራእ. 21፥2፣ 10-11፤ 22፥1-2።
2. የሞት እና የመልካምና ክፉ መንገድ መጠናቀቅ የእሳት ባሕር ነው—19፥20፤ 20፥10፣ 14-15፤ 21፥8።

### II. የእግዚአብሔር ውጥን በመልካም እና በክፉ እውቀት ዛፍ መስመር ላይ ያለ ኢዮብ ሳይሆን በሕይወት ዛፍ መስመር ላይ ያለ ኢዮብ ይኖረው ዘንድ ነበር፦

ሀ. የኢዮብ እና የጓደኞቹ አመክንዮ በመልካም እና በክፉ እውቀት ዛፍ መስመር መሠረት ነበር—ኢዮብ 2፥11—32፥1።

ለ. ኢዮብ፣ እንደ ጓደኞቹ፣ የእግዚአብሔርን ኢኮኖሚ ባለማወቅ በትክክልና በስህተት እውቀት ተይዞ ነበር—4፥7-8።

ሐ. ኢዮብና ጓደኞቹ በመልካም እና በክፉ እውቀት ዛፍ ክልል ውስጥ ነበሩ፤ እግዚአብሔር ከዚያ ክልል ሊያድናቸውና በሕይወት ዛፍ ክልል ውስጥ ሊያኖራቸው እየሞከረ ነበር—1፥1፤ 2፥3፤ 19፥10።

መ. ኢዮብን በማደቡ የነበረው የእግዚአብሔር ዓላማ እግዚአብሔርን በሙላት ያገኝ ዘንድ ከመልካምና ክፉ መንገድ ወደ ሕይወት መንገድ እርሱን ማዞር ነበር—42፥1-6።

### III. የሕይወት ዛፍ ራእይ—የእግዚአብሔር በክርስቶስ ምግባችን የመሆኑ ራእይ— ያስፈልገናል—ዘፍ. 2፥9፤ ራእ. 22፥1-2፣ 14፦

ሀ. የሕይወት ዛፍ ሦስታንዱ አምላክ በክርስቶስ፣ በምግብ መልክ እንደ ሕይወት ራሱን ወደ መረጣቸው ሰዎች ውስጥ ለማደል መሆኑን ያመለክታል—ዘፍ. 2፥9።

ለ. የሕይወት ዛፍ የአጽናፍ-ዓለም ማዕከል ነው፦

1. በእግዚአብሔር ዓላማ መሠረት፣ ምድር የአጽናፍ-ዓለም ማዕከል ናት፣ የዔድን ገነት የምድር ማዕከል ናት፣ የሕይወት ዛፍ የዔድን ገነት ማዕከል ነው፤ በመሆኑም፣ የአጽናፍ-ዓለም ማዕከል የሕይወት ዛፍ ነው።
2. ለእግዚአብሔር እና ለሰው ከሕይወት ዛፍ የበለጠ ማዕከላዊ እና ወሳኝ የሆነ ምንም ነገር የለም—3፥22፤ ራእ. 22፥14።

ሐ. ክርስቶስ የሕይወት ዛፍ ስዕል መፈጸም መሆኑን አዲስ ኪዳን ይገልጣል—ዮሐ. 1፥4፤ 15፥5።

መ. በዮሐንስ ወንጌል የተገለጡት ሁሉን-ያካተተው ክርስቶስ ገጽታዎች ሁሉ የሕይወት ዛፍ ውጤት ናቸው—6፥48፤ 8፥12፤ 10፥11፤ 11፥25፤ 14፥6።

ሠ. የሕይወት ዛፍ ድሰታ በእግዚአብሔር የተዋጁት ሁሉ ዘላለማዊ እድል ፈንታ ይሆናል—ራእ. 22፥1-2፣ 14፦

1. ከመጀመሪያው እግዚአብሔር ለሰው የወጠነውን የሕይወት ዛፍ ለዘላለም ይፈጽማል—ዘፍ. 1፥26፤ 2፥9።
2. የሕይወት ዛፍ ፍሬዎች በእግዚአብሔር ለተዋጁ ለዘላለም ምግብ ይሆናሉ፤ እነዚህ ፍሬዎች በየወሩ በመፍራት ያለማቋረጥ ትኩስ ይሆናሉ—ራእ. 22፥2።

## IV. ዳግም ስንወለድ፣ ክርስቶስ ራሱን እንደ የሕይወት ዛፍ ወደ እኛ ውስጥ ተከለ—ዮሐ. 1፥12-13፤ 3፥3፣ 5-6፣ 15፤ 11፥25፤ 15፥1፣ 5፦

ሀ. በተግባራዊ ኑሮአችን፣ በመልካምና ክፉ እውቀት ዛፍ መስመር እንጂ በሕይወት ዛፍ መስመር ላይ ላንሆን እንችላለን—ምሳ. 16፥25፤ 21፥2።

ለ. ኢዮብ በስነ ምግባር ክልል ውስጥ ያለን ነገር ተከታተለ፣ እኛ በክርስቶስ ያለን አማኞች ግን በእግዚአብሔር ክልል ውስጥ ያለን ነገር ልንከታተል ይገባል—1 ቆሮ. 15፥28፤ ኤፌ. 3፥16-21።

ሐ. በየዕለት ኑሯችን ሕይወትን በሚሰጠው መንፈስ ክልል ውስጥ እንጂ በመልካምና ክፉ እውቀት ዛፍ ክልል ውስጥ መሆን የለብንም—1 ቆሮ. 15፥45፤ ሮሜ 8፥2።

መ. የእግዚአብሔር ውጥን ከእርሱ ጋር ፈጽሞ አንድ የሆንን ሰዎች እንሆን ዘንድ እኛን ማፍረስ እና እንደ ሕይወታችን እና ባሕሪያችን በራሱ መልሶ መገንባት ነው—2 ቆሮ. 1፥9፤ 4፥14።

© 2026 Living Stream Ministry

መልእክት አምስት

**እግዚአብሔር በኢዮብ ዘንድ የነበረው ውጥን—መልካም ሰው አምላክ-ሰው እንዲሆን**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፡- ኢዮብ 1፥1፣ 8፤ 2፥3፣ 9፤ 27፥5፤ 31፥6፤ 42፥5-6

I. **ስልሳ ስድስት መጻሕፍት የያዘው መጽሐፍ ቅዱስ ለአንድ ነገር ብቻ ነው—ክርስቶስን እንኖረው እና ክርስቶስን እንገልጠው ዘንድ እግዚአብሔር ሕይወታችን፣ ባሕርያችን እና ሁሉ ነገራችን ለመሆን በክርስቶስ እንደ መንፈስ ራሱን ወደ እኛ ውስጥ ለማደሉ ነው—ኤፌ. 3፥16-17፤ ፊልጵ. 1፡21፡-**

ሀ. ይህ ሕይወታችንን የሚገዛ መርህ ሊሆን ይገባል—ዮሐ. 6፥57።

ለ. በተግባራዊ መንገድ፣ ይህ ለድሰታችን የዛሬው የሕይወት ዛፍ ሊሆን ይገባል—ራእ. 22፥14።

II. **ኢዮብ በፍጹምነቱ፣ በቅንነቱ እና በሐቀኝነቱ ራሱን የሚገልጥ መልካም ሰው ነበር—ኢዮብ 27፥5፤ 31፥6፤ 32፥1፡-**

ሀ. ፍጹም መሆን ከውስጡ ሰው ጋር የተገናኘ ነው፣ ቅን መሆን ከውጪው ሰው ጋር የተገናኘ ነው—1፥1።

ለ. ኢዮብ ሐቀኝነት ያለው ሰው ነበር፤ ሐቀኝነት ፍጹም እና ቅን የመሆን ጥቅል ድምር ነው—2፥3፣ 9፤ 27፥5፤ 31፥6፡-

1. ከኢዮብ አንጻር፣ ሐቀኝነት እርሱ የሆነው ነገር ጥቅል መገለጥ ነው።
2. በጠባይ፣ ኢዮብ ፍጹም እና ቅን ነበር፣ በስነምግባሩ፣ ከፍተኛ ደረጃ ያለው ሐቅ ነበረው።

ሐ. ኢዮብ በአዎንታዊ መልኩ እግዚአብሔርን ፈራ፥ በአሉታዊ መልኩ ከክፋት ራቀ—1፥1፡-

1. እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረው እንዲፈራው እና ምንም ስህተት እንዳይፈጽም ብቻ አልነበረም፤ ይልቁንም፣ ሰው እግዚአብሔርን ይገልጥ ዘንድ እግዚአብሔር ሰውን በመልኩ እንደምሳሌው ፈጠረው—ዘፍ. 1፥26።
2. እግዚአብሔርን መግለጥ እግዚአብሔርን ከመፍራትና ከክፋት ከመራቅ ይበልጥ ከፍ ያለ ነው።
3. ኢዮብ በፍጹምነቱ፣ በቅንነቱ እና በሐቀኝነቱ የደረሰበት ነገር ሙሉ በሙሉ ከንቱ ነበር፤ ያ የእግዚአብሔርን ዓላማ አልፈጸመም፣ የእግዚአብሔር መሻትንም አላረካም፣ ከዚህም የተነሣ ለኢዮብ በፍቅር ግድ ተሰኝቶ ነበር—ኢዮ. 1፥6-8፤ 2፥1-3።

መ. ኢዮብ የሚያስፈልገው ነገር እንደነበር የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ነበር—በውስጡ እግዚአብሔር አልነበረውም፤ ስለዚህ፣ እግዚአብሔር ለዓላማው መፈጸም ይገልጠው ዘንድ ኢዮብ እርሱን እንዲያገኝ ፈለገ—42፥5-6።

III. **የእግዚአብሔር ውጥን ኢዮብ እግዚአብሔርን በባሕርያቱ የሚገልጠው አምላክ-ሰው እንዲሆን ነበር—22፥24-25፤ 38፥1-3፡-**

ሀ. ኢዮብ በፍጹምነቱ፥ በጽድቁ እና በሐቀኝነቱ ከደረሰባቸው ነገሮች ምትክ እግዚአብሔርን ያገኝ ዘንድ እግዚአብሔር ኢዮብን ወደ ሌላ ክልል፣ ወደ እግዚአብሔር ክልል አስገባው—42፥5-6።

ለ. እግዚአብሔር በኢዮብ ዘንድ የነበረው ውጥን እርሱን መጨረስ፣ በፍጹምነትና በቅንነት በከፍተኛው የስነምግባር ደረጃ የደረሰባቸውን ነገሮች፣ ስኬቶቹን መግፈፍ ነበር—31፥6።

ሐ. የእግዚአብሔር ውጥን በእግዚአብሔር ተፈጥሮ እና ባሕርያት የታደሰ ኢዮብን ይገነባ ዘንድ ፍጹሙን እና ቅኑን ተፈጥሮአዊ ኢዮብ ማፈራረስ ነበር—1፥6-8፤ 2፥3-6።

መ. የእግዚአብሔር ውጥን ኢዮብን በክርስቶስ ለእግዚአብሔር መገለጥ የእግዚአብሔር ሙላት ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር አካል መልበስ በሆነው በክርስቶስ የተሞላ የእግዚአብሔር ሰው ማድረግ ነበር—1 ጢሞ. 6፥11፤ 2 ጢሞ. 3፥17።

ሠ. የእግዚአብሔር ኢዮብን መግፈፍና መጨረስ የተከናወኑት፣ ኢዮብን በእግዚአብሔር በራሱ መልሶ ለመገንባት መሠረት እና መንገድ ይኖረው ዘንድ እርሱን ለማፈራረስ ነበር፤ ይህም ኢዮብ እግዚአብሔርን ለመግለጥ የእግዚአብሔር ሰው፣ በተመላኪነቱ ሳይሆን በሕይወቱና በባሕርይው ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ዓይነት ይሆን ዘንድ ነው—ኤፌ. 3፥16-21።

**IV. በክርስቶስ እግዚአብሔር ወደ ሰው ውስጥ ተቀናብሯል፣ ሰው ወደ እግዚአብሔር ውስጥ ተቀናብሯል፣ እግዚአብሔር እና ሰውም አምላክ-ሰው ተብሎ የሚጠራው አንድ አካል ለመሆን በአንድ ላይ ተዋሕደዋል—ማቴ. 1፥21፣ 23፤ ሉቃ. 1፥35፤ ቲቶ 2፥13፤ 1 ጢሞ. 2፥5፦**

ሀ. ብዙ አምላክ-ሰዎች፣ የእግዚአብሔር ብዙ ልጆች የክርስቶስ፣ የመጀመሪያው አምላክ-ሰው መጨመር፣ ርቢ፣ ብዜትና መቀጠል ናቸው—ዮሐ. 12፥24፤ ዕብ. 2፥10፤ ሮሜ 8፥29።

ለ. አምላክ-ሰው የእግዚአብሔርን ሕይወትና ባሕርይ የሚካፈል፣ ከዚህም የተነሣ በሕይወቱና በባሕርይው ከእግዚአብሔር ጋር አንድ የሚሆን፣ በዚህም እግዚአብሔርን የሚገልጥ ነው—ዮሐ. 3፥15፤ 2 ጴጥ. 1፥4፤ 1 ቆሮ. 6፥17።

ሐ. አምላክ-ሰው የእግዚአብሔርን ሕይወትና ባሕርይ የያዘ የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆን ከእግዚአብሔር ተወልዷል—ዮሐ. 1፥12-13፤ 3፥6፦

1. አምላክ-ሰው ሁለት ሕይወቶች፣ የሰብዕና እና መለኮታዊው ሕይወት፣ ሁለት ባሕርያት፣ ሰብዕና እና መለኮት አሉት።
2. አምላክ-ሰው የሕይወት-ሰው ነው—1 ዮሐ. 5፥11-13፤ ሮሜ 8፥2፣ 6፣ 10-11።
3. አምላክ ሰው የወርቅ-ሰው ነው—ዘጸ. 25፥11፤ 1 ጴጥ. 1፥7፤ ራእ. 3፥18፤ 21፥18።

መ. አምላክ-ሰው በእግዚአብሔር የተቀናበረ፣ እግዚአብሔር እንደ ሕይወቱ፣ የሕይወት አቅርቦቱ እና ሁሉ ነገሩ ያለው ነው፤ ስለዚህ፣ አምላክ-ሰው ሰው፣ ሆኖም አምላክ፣ አምላክ፣ ሆኖም ሰው ነው—ኤፌ. 3፥16-17።

ሠ. አምላክ-ሰው አዲስ ፍጥረት እና በክርስቶስ የእግዚአብሔር ጽድቅ ነው—2 ቆሮ. 5፥17፣ 21።

ረ. አምላክ-ሰው በማንነቱ ሁሉ፣ ከልቡ፣ ከነፍሱ፣ ከአእምሮው እና ከኃይሉ ጌታን ይወዳል—ማር. 12፥30።

ሰ. አምላክ-ሰው በሥጋ አይታመንም፣ ራሱን ይክዳል፣ ክርስቶስን ለመኖርም መንፈሱን ያንቀሳቅሳል—ፊልጵ. 3፥3፤ ማቴ. 16፥24፤ 1 ጢሞ. 4፥7፤ ፊልጵ. 1፥21።

ሸ. አምላክ-ሰው የእግዚአብሔር ቃል ያለው፣ የእግዚአብሔርን እስትንፋስ ወደ ውስጡ የሚተነፍስ የእግዚአብሔር ሰው ነው—1 ጢሞ. 6፥11፤ 2 ጢሞ. 3፥16-17።

ቀ. አምላክ-ሰው ኢ-ጥገኛ ግለሰብ እንዳልሆነ፣ ነገር ግን ከብዙዎች የሆነው አምላክ-ሰው—የክርስቶስ አካል፥ የአንዱ አዲሱ ሰው— ክፍል እንደሆነ ይገነዘባል—1 ቆሮ. 12፥12-13፤ ኤፌ. 4፥16፤ ቆላ. 3፥10-11።

*© 2026 Living Stream Ministry*